የሰ/መ/ቁ. 22514

መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

2. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

3. አቶ ታፈሰ ይርጋ

4. አቶ ዓሊ መሐመድ

5. አቶ ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** 1ኛ/ አቶ ኩራት ተገኝ

2ኛ/ አቶ መርሻ ኩራት

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ጥፋተኝነትንና ቅጣትን የተመለከተ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው ተጠሪ /ዓቃቤ ሕግ/ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ የአሁን አመልካቾች በቂም በቀል ተነሣስተው ሰው ለመግደል በማሰብ ጌጡ ተስፋው እና ብርሌ ባላምባራስ የተባሉ የግል ተበዳዮችን ራስ ራሳቸውን በድንጋይና በዱላ ከደበደቧቸው በኋላ 1ኛ ተከሣሽ በያዘው አጭር አልቤን መሣሪያ አንድ ጥይት ተኩሶ 2ኛ የግል ተበዳይን የግራ ፊቱን በማቁሰሉ በፈፀሙት በግብረ-አበርነት ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በዓቃቤ የቀረበውን የሰውና የሕክምና ማስረጃ ሰምቶ ተከሳሾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 141 መሠረት በነፃ ያሰናበታቸው ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዓቃቤ ሕግ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ተከሣሾች በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የተመሰከረባቸው ስለሆነ በተመሰከረባቸው መጠን ሊከላከሉ ይገባል፣



በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተከሣሳሾችን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት የመሰለውን ይወስን በማለት ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መለሰው፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት ፍ/ቤትም የመከላከያ ምስክሮቹን አዳምጦ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል በመከላከያ ምስክሮቹ ቃል ስላልተስተባበለ ተከሳሾች /የአሁን አመልካቾች/ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው፣ ስለሆነም እያንዳንዳቸው በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወሰነ፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ፍርዱን አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካቾች ፈፀሙት በተባለው አስቀድሞ በማሰብ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉት በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡

አመልካቾች የተከሰሱትም ሆነ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡት አስቀድሞ በማሰብ ወይም ምክንያት በማድረግ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡ ምንም እንኳ በዓቃቤ ሕግ በምስክርነት የተቆጠሩት የግል ተበዳዮች ድርጊቱ የተፈፀመው በድንበር ግጭት ምክንያት የአሁኖቹ አመልካቾች ቂም በቀል ይዘው ነው የሚል የምስክርነት ቃል ስለመስጠታቸው በስር ፍ/ቤት የውሣኔ ሐተታ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ይህ አባባል ከእነሱ ቃል በስተቀር በሌላ ገለልተኛ ማስረጃ ተደግፎ አለመገኘቱን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዓቃቤ ሕግ የቀረበው የሰውና የሕክምና ማስረጃ ያረጋገጠው ነገር በግል ተበዳዮች ላይ "የአጥንት ስብራት የሌለበት ቀላል እብጠትና ደም ያለው ምልክት" መሆኑ ታውቋል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ተፈፀመ የተባለው ተግባር ተራ የሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል